# 2ኛ የዮሐንስ መልእክት

፩-፫ ከእግዚአብሔር አብና ከአብ ልጅ ከኢየሱስ ክርስቶስ
ጸጋና ምሕረት ሰላምም በእውነትና በፍቅር ከእኛ ጋር ይሆናሉ።
፬ ትእዛዝን ከአብ እንደ ተቀበልን ከልጆችሽ በእውነት የሚሄዱ
አንዳንዶችን ስለ አገኘኋቸው እጅግ ደስ ብሎኛል። ፭ አሁንም፥
እመቤት ሆይ፥ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ እለምንሻለሁ፤
ይህች ከመጀመሪያ በእኛ ዘንድ የነበረች ትእዛዝ ናት እንጂ
አዲስ ትእዛዝን እንደምጽፍልሽ አይደለም። ፮ እንደ ትእዛዛቱም
እንሄድ ዘንድ ይህ ፍቅር ነው፤ ከመጀመሪያ እንደ ሰማችሁ፥
በእርስዋ ትሄዱ ዘንድ ትእዛዙ ይህች ናት። ፯ ብዙ አሳቾች
ወደ ዓለም ገብተዋልና እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ
መጣ የማያምኑ ናቸው፤ ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚው
ነው። ፰ ሙሉ ደመወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሠራችሁትን
እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ፱ ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም
ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ
ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት። ፲ ማንም ወደ እናንተ
ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት
ሰላምም አትበሉት፤ ፲፩ ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው
ይካፈላልና። ፲፪ እንድጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር ሳለኝ
በወረቀትና በቀለም ልጽፈው አልወድም፥ ዳሩ ግን ደስታችሁ
ፍጹም እንዲሆን ወደ እናንተ ልመጣ አፍ ለአፍም ልናገራችሁ
ተስፋ አደርጋለሁ። ፲፫ የተመረጠችው የእኅትሽ ልጆች ሰላምታ
ያቀርቡልሻል።

# መጽሐፍ ቅዱስ
# The New Testament in the Amharic language of Ethiopia

copyright © 1962, 2003 United Bible Societies

Language: አማርኛ (Amharic)

**Amharic NT**

Revised Amharic Bible in XML (2003).

Printed version by United Bible Societies (C)1962.

E-Text in transliterated ASCII format by Lapsley/Brooks Foundation 1994.

Unicode UTF-8 transformation and XML-tagging by Dirk Röckmann 2003 (www.nt-text.net).

With kind permission of the Bible Society of Ethiopia.

Every non-commercial work using this data in any form must fully include this copyright statement!

Every commercial use of parts or the complete data in any form needs written permission of the Bible Society of Ethiopia!

2014-09-09

---

PDF generated using Haiola and XeLaTeX on 11 Nov 2022 from source files dated 9 Oct 2020
2432e07d-4260-5d76-afcb-ce35bd1c48b7